በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

የተከበራችሁና የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች፣ ለፍቅሩና ለቸርነቱ ወሰን የሌለው አምላካችን መድኃኔዓለም ክርስቶስ እንኳን ለበዓለ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ።

## *«ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት»*

ኃጢአትን ለማስተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን። ጥምቀት ከእግዚአብሔር የተሰጠን የዳግም መወለጃ ጸጋ ነው። ሰው በሥጋ ሲወለድ በሚታይና በሚዳሰስ ግዙፍ አካል ይወለዳል፤ በጥምቀት ሲወለድ ግን በማይታይ ድንቅና ረቂቅ በሆነ ምሥጢር ከመንፈስ ቅዱስ ይወለዳል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ይህን የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ቁልፍ የሆነውን ጥምቀታችንን ቀድሶ ይሰጠን ዘንድ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆልናል። «ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ መሬታዊ» እንዳለ ቅዱስ ያሬድ።

የጌታችንን በዓለ ጥምቀት የምናከብረው ዳግም ለመጠመቅ አይደለም፤ በዓሉን የምናከብረው ጌታችን የሰጠንን ታላቅ ጸጋ በማስታወስ ከበዓሉ ማግኘት የሚገባን ጸጋና በረከት ለማግኘት ነው። እኛስ ጥምቀት የማትደገም፣ የማትከለስ አንዲት መሆንዋን እናምናለን፤ በ፵ እና በ፹ ቀናችን በተጠመቅን ጊዜ ያገኘነው ዳግም ልደት የማይሻር ፍጹም ጸጋ ነው። ዮሐ ፫፥፫-፯። የሰው ልጅ ዳግም ልደት፣ የአዳም ቀዳማዊ ልደት ምሳሌ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ የተጠመቀው፡- ፩ኛ- የአማናዊ ጥምቀታችንን መሠረት ለመጣል፣ ፪ኛ- ጥምቀታችንን ለመቀደስ ነው። እሱ ጥምቀታችንን ቀድሶ ክብረ መንግሥተ ሰማያት የምናገኝበትን ዳግም ልደት (የጥምቀት ጸጋ ሰጥቶናል)። እኛ ስንጠመቅ ክብር እናገኛለን፤ ዳግመኛ ተወልደን የእግዚአብሔር ልጆች ለመባል እንበቃለን፤ አዳም ከመሳቱ በፊት አግኝቶት የነበረውን የልጅነት ክብር እናገኛለን። ጌታችን ግን የክብር ባለቤት በመሆኑ፣ በመጠመቁ ከበረ አይባልም፤ የለበሰው ሥጋ የከበረው በተዋሕዶ ነው፤ ማለትም አካላዊ ቃል በማኅጸነ ድንግል በተቀረጸበት ጊዜና ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋና ነፍስ በተዋሐደ ጊዜ ሰው አምላክ ሆኖዋል፤ አምላክም ሰው ሆኖአል። ሥጋ በተዋሕዶ ከበረ የሚባለው ከፅንስ ጀምሮ ነው። ስለሆነም የክርስቶስ ሰውነት መለኮት ተዋሕዶት በፍጹም ክብር ለመለኮት በሚገባ ክብር የተወለደ በመሆኑ በመጠመቁ ያገኘው ወይም የሚጨመርለት ምንም ዓይነት ክብር አልነበረም። «አኮ ፈቂዶ ለተጠምቆ ኣላ ከመ የሀበነ ሱታፌ ንጽሕ» እንዳለ ሊቁ። ሃ. አበው።

ጌታችን በ፴ ዓመቱ የመጠመቁ ምክንያትም የሚሠራቸው ሥራዎች ሁሉ በጊዜ የተቀመሩ ስለነበሩ ነው፤ የጥምቀቱ ሥራ የሚከናወነው በዮሐንስ እጅ ስለነበረና ዮሐንስም የማጥመቅ ሥራውን የጀመረው ጌታችን ፴ ዓመት ሲሆነው ስለነበረ ብቻ ነው። የጌታ ጥምቀት ከዕድሜ ገደብ ጋር የሚያገናኝ ምንም ዓይነት ምክንያትና ምሥጢር የለውም።

ጌታችን በመጠመቁ ጥምቀታችንን ባረከልን፤ ቀደሰልን። በጥምቀቱ ዳግመኛ እንድንወለድ አደረገ እንጂ እሱ የጐደለበት ኖሮ የተጠመቀ አይደለም፤ ጌታ በመጠመቁ ክብር አገኘ የሚሉ የጌታን ፍጹም አምላክነት ካለመረዳት የሚናገሩት ክሕደት ነው። ጌታ በ፴ ዓመቱ ስለተጠመቀ ሰው እንደ ጌታ በ፴ ዓመቱ መጠመቅ አለበት ብሎ ማመንም፣ የአዳምን ስሕተት መልሶ ማምጣት ነው። ጌታ ፈጣሪ በመሆኑ አምላክ ነው። ለፍጡሩ ጸጋን ያድላል። ሰው ፍጡር በመሆኑ ከፈጣሪው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋን ይቀበላል። ስለሆነም ጸጋ ሰጪውንና ጸጋ ተቀባይን አንድ አድርጎ መመልከት ፍጹም ስሕተትና ክሕደት ነው።

መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ፣ የማጥመቅ ሥራውን ሲጀምር በይሁዳ በረሃ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ያስተምር ይገሥፅ ነበር። ገዳመ ይሁዳ የተባለው በትዕቢት የደነደነው ልበ አይሁድ ነው። በበረሃ እህል፣ ተክል እንደማይገኝ ሁሉ በልበ አይሁድም ምግባረ ሃይማኖት አልተገኘምና «ጺሑአ ፍኖቶ ለእግዚአብሔር ወዓርዩ መጽያሕቶ፣ ማለት የእግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ፤ መንገዱንም አስተካክሉ፤ (የቀና አድረጉ) ጐድጓዳው ይሙላ ተራራውና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይበል፤ ሰንካልካላው መንገድ ቀና ይሁን፤ ጠማማው ይስተካከል።» እያለ ያስተምር ነበር።

ቅዱስ ዮሐንስን ያሳሰበው የጠማማው መንገድ፣ ወይም የገደሉና የጉድጓዱ ጉዳይ አልነበረም ያሳሰበው ለእግዚአ ብሔር ማደሪያነት ምቹ ያልሆነ ያልተስተካከለ የሰው ልጅ ልቡና ነው፤ ያሳሰበው። የሰው ልጅ ከንቱ አስተሳሰብ፣ ትዕቢት፣

ተንኮል፣ ክፋት፣ ምቀኝነት ፈሪሳዊ አስተሳሰብና በአጠቃላይ የኃጢአት ምንጭ የሆነ የሰው ልጅ ግብዝነት ነው። እርግጥ ነው ቅዱስ ዮሐንስ የጠቀሳቸው መሠረታዊ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር በሰው ልብ ያድር ዘንድ ለማድረግ የማይመቹ ናቸውና ሁሉም ተወግደው የሰው ልብ በእውነት፣ በቀናነትና በንጽሕና ሆኖ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት ሊዘጋጅ ይገባል።

የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነው የክርስቲያን ልብ ከክፋት፣ ከተንኮል ከቂም፣ ከበቀል፣ ከአምልኮ ጣዖት፣ ከሐሰት ከስርቆትና ከዝሙት ነፃ ሊሆን ይገባል። በኃጢአት ወድቄያለሁ የሚል ሰው፣ በአንብዓ ንስሐ ታጥቦ በቅድስና እንዲኖር ማድርግ የሚችል አምላኩን በማመን ሥርየተ ኃጠአትን በተስፋ መጠበቅ አለበት።

ከጥምቀተ ዮሐንስ የምንማረው ሌላው ትልቅ ቁምነገር ደግሞ፣ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ በክርስቶስ ተሽሮ በፍዳ ተይዞ የነበረው ዓለም ነፃ መውጣቱን ነው። የሰው ልጅ ተጭኖት ከነበረው የዲያቢሎስ የባርነት ቀንበር ነፃ መውጣቱንና በተራራ የተመሰለው ዲያብሎስ ወድቆ መዋረዱን ነው። ቆላ ፪፥፲፬፣ ኤፌ ፪፥፲፫።

ጌታችን የተጠመቀው በዮርዳኖስ ነው፤ ይኸውም ምሳሌውና ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ሲሆን ምሥጢሩም ባሕረ ዮርዳኖስ፣ ከላይ ምንጩ አንድ እንደሆነ የሰው ሁሉ ምንጩ አዳም መሆኑን፤ ዝቅ ብሎ በደሴት እንደሚከፈል እስራኤል በግዝረት አሕዛብ በቍልፈት (ባለመገረዝ) የመለያያቸው ምሳሌ ነው። ከታች ወርዶ እንዲገናኝ ሕዝብና አሕዛብ በክርስቶስ ጥምቀት አንድ የመሆናቸው ምሳሌ ነው።

ሌላው ደግሞ ዮርዳኖስ ሕሙማንን የመፈወስ ኃይል ነበረው። ኢዮብን፣ ለምፃሙ ንዕማንንና ዕውር ሆኖ የተወለደውን በምሳሌነት ማየት ይቻላል። ጌታችንም፣ ፍጥረቱ ሁሉ ከደዌ ነፍስ የሚፈወሰው በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ ማግኘት የሚችለው እርሱ በዮርዳኖስ ተጠምቆ ጥምቀታችንን ከባረከልንና ከቀደሰልን በኋላ መሆኑን የሚያስተምር ታላቅ ምሥጢር ነው።

አዳም አባታችንን ከነልጆቹ ከማእሰረ ሰይጣን የፈታና ዓለምን በጥምቀቱ የቀደሰ አምላካችን ክርስቶስ በረከተ ጥምቀቱ ያሳትፈን፤ አሜን።

ሊቀ ካህናት ኃይለሥላሴ ዓለማየሁ ደስታ
የዴንቨር ኮሎራዶ፣ የደብረ ሰላም መድኃኔዓለም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪና
የሰሜን ምዕራብ አሜሪካ ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት
ዋና ሥራ አስኪያጅ